# አበጀ ይበለን!!

አስራደው (ከፈረንሳይ)

ኢትዮጵያዊነታችንን አቅልለን፣
ትንሽ ሆነን፣ ዝቅ ብለን ከተዋረድን፣
በነሱ እግር ስር ወድቀን፣
ነጭ አምላኩ ሆነን፣
መብታችንን ከነሱ ከለመን፣
እሰይ አበጀ ይበለን!
ያዋርዱ ያበሻቅጡን፣
መዘባበቻ መሳቂያ ያድርጉን።
ጀግንነቱ ተዘንግቶን፣
አሻፈረኝ ማለት ገዶን፣
ታሪክ ፍቀን፣
አገር ንደን፣
አዋርደነው ክብራችንን፣
ውለን ካደርን ለሆዳችን፣
ጫማቸው ስር ተንበርክከን፣
ተለማምጠን ከተማጠን፣
ዴሞክራሲ እንዲሰጡን፣
አበጀ ይበለን!
ያዋርዱን! ይናቁን!
ይሳለቁ! ያሹፉብን!
ይዛበቱ! ያበሻቅጡን።
አበው እንዳሉት፣
ያባይን ልጅ ውሃ ጠማት፣
የሳጪን ልጅ  ቅማል በላት፣
ከቀያችን ዓባይ ፈልቆ፣
ለግብፅ ሲያድል መሬት ገዝቶ፣
ምድራችንን አምክነን፣
የነጭ ስንዴ ተመጽውተን።
አሁን ደግሞ ነፃነትን አዘርፈን፣
እንደ ሰንዴ እንዲለግሱን፣
እንለምናለን ተንበርክከን፣
ነጭ አምላኪዎች ሆነን።
ይበልን ይናቁን!
ያበሻቅጡን ያዋርዱን!
ቁልቁል ይመልከቱን!
ያሽካኩ ይሳቁብን!
መቀለጃ ያድርጉን፣
እኛው ወደን ከተጃጃልን!
መተማመን መከባበር፣
መደማመጥ መነጋገር፣
መማር መማማር፣
መወያየት ማመዛዘን፣
ተስኖን ከተቃቃርን፣
ከተናከስን ከተቧጨቅን፣
ይበለን ይናቁን!
ያበሻቅጡን! ያዋርዱን!
ያሳለቁ! ያፊዙብን!
ወደን ከተዋረድን!

(ነፃነታችንን ለተዘረፍነው ወገኖች በሙሉ (የካቲት 24 ቀን፣ 1999 ዓ. ም. / Feb 03, 2007)

Posted on www.debteraw.com on 04 March 2007 by courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com